# ለደርግ ይቅርታ መጠየቅ በኢትዮጵያ ህዝብ ደም መቀለድ

የመንግሥቱ ኃይለ ማሪያም መንግሥት 17 ዓመት ሙሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ጭፍጨፋ ግፍና መከራ በህይወት ያለ ማንም ኢትዮጵያዊ አይረሳዉም። በስንት መቶ ሺህ የሚቆጠር ኢትዮጵያውያን የሃገሪቱን ንጹህ ዜጋ ማለትም፣ የተማረው ሊቅ አስተማሪና ተማሪ፤ ዳር ድንበሯን በማስጠበቅ ዉድ ህይወታቸውን ለማሳለፍ በየጠረፉ የኖሩና የሠሩ፤ እስከ ለጋ ሕጻናት ሳይቀር ሌሊት በቁር ቀን በጠራራ ጸሓይ በመትርጌስ እየተደብደቡ በቡል ዶዘር ሬሳቸው ወደገደል ተጥሎ ያለቀውን ህዝብ ስንዘከር፤ ያ የደርግ ዘመን፣ “ዘመነ መከራ” ተብሎ መጠራት ያለበት ነው። አሁን ታዲያ ለነዚህ አረመኔዎች ይቅርታ እንዲደርግላቸው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከሌሎች የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመተባበር በአባ ጳውሎስ መሪነት ከፍተኛ ዉትወታ እየተደረገ መሆኑን እናነባለን፡ በጣም ይገርማል፤ በጣምም ያበሳጫል።

የቀድሞው ወታደራዊ ጁንታ በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሰው ሰቆቃ ከሱ ጊዜ በፊት በማንኛውም የግዛት ዘመን ትይቶ አይታወቅም፤ እነዚህ በሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች የፈጽሙት በደል በዓይነትም ሆነ በመጠን እጅግ ሰፊና ከባድ፤ ዘወትር ሲያስቡት ለህሊና የሚሰቀጥጥ እኩይ ተግባር ነው። በዚቺው አገር ላይ ዕውነተኛ ፍርድ ቢኖር ኖሮ እነዚህ አረመኔዎች አሁን በህይወት መቆየት አልነበረባቸውም፤ ዳሩ ግን ምን ይሁን፤ አሁን በቦታው ተተክቶ በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት ራሱ ከርሱው በፊት ከነበረው በከፋ ሁኔታ ኢትዮጵያን በዘርና በቋንቋ ለያይቶ ህዝቡን የመሬት ሥቃይ እያሳዬ ስለሚገኝ፤ ነግ በእኔ የሚለውን በታሳቢነት በመውሰድ ሰዎቹ ከሞት ፍርድ በኋላ ከ 10 ዓመት በላይ በእሥር ላይ ሆነው የነጻነት አየር እየተነፈሱ ይገኛሉ።

ባለፈው ጊዘ ከአንድ ድህረ-ገጽ ላይ እንዳነበብኩት፤ የአባ ጳውሎስ ኮሚቴ የ60ዎቹን የቀ. ኃ. ሥ. ባለሥልጣናት ቤተሰቦችን ለማነጋገር ቀጠሮ ይዞ ነበር፡፡ ለመሆኑ ባለፈው 17 ዓመት የደርግ ዘመን የተገደሉት እነዚህ 60 ሰዎች ብቻ ናቸው? ወይስ ደግሞ ለሞትና ለአሟሟት የተለየ ደረጃ አለው? ማን ነው ይቅርታ የሚጠየቀው? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ናት ወይስ በጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ? በመጀመሪያ ይህ ጥያቄ ነው መመለስ ያለበት፤ በሁለተኛ ደርጃ፤ ለመሆኑ ይህንን ሃሣብ ማንነው ያመነጨው? ከመንግሥት ወገን ነው ወይስ ከቤተክርስትያን ከራሷ?በዚያም ብሎ በዚህ፣ ሃሣቡ ባሁኑ ወቅት እንዲነሣ የተደረገበት ግልጽ ምክንያት አለው፤ ይኸውም አሁን ያለው የወያኔ መንግሥት የቤተክርስቲይኒቱን መሪ ጭምር በሃገሪቱና በህዝቡ ላይ እያደርሱ ያለው ግፍና መከራው መስፈሪያው ሞልቶ ወደመፍሰሱ ደረጃ ላይ ስለደረሰ፤ ነግ በእኔን ከግንዛቤ በማስገባት የሚደረግ መሯሯጥ ሊሆን እንደሚችል የማንኛውም ተራ ሰው ግምት ነው።

ይህንኑ ርዕስ በተመለከተ አንዳንዶች የሚሰጡትን አስተያየት አንብቤአለሁ፤ እንዲያውም የአንዱን ትችት መጥቀስ እፈልጋለሁ፤ “ ... ጥፋተኛ ከጥፋቱ ቢፀፀትና ከልቡ ምህረት የጠየቀ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅር የማይልበት ምክኒያት የለውም። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ይህቺ ምድር ይቅርታን የማታውቅ፥ ጥፋቱን አምኖ ለተጸጸተና፥ አጥፍቻለሁ፣ ስቻለሁና ፍርድን እሻለሁ ሲል ድምጹን ለሚያሰማና ራሱን ላዋረደ አቤት የማትል በምሕረት ዘርዋን የማትቀበል ብትሆን ግን ወልዳ መቅበር ዕጣ ፈንታዋ ይሆናል።”

ይህ አባባል ሊሠራ የሚችለው በአንድ አካባቢ ዉስጥ በአጋጣሚ በሁለት ወይም ከዚያ በበለጡ ሰዎች መካከል የተፈጸመ ዕለታዊ የድብደባ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ቀላል ዓይነት ወንጀል ቢሆን ነው፤ በርግጥ እንደዚህ የመሰለ የፍርድ ቅጣት ላይ ያለ ሰው ከተጣላው ሰው ወይም ቤተሰብ ዘንድ ይቅርታ መጠየቅና ተጠያቂውም ወገን ይቅርታ ቢያደርግ የመጽሃፉ ትዕዛዝ በሥራ ላይ ሊውል ይችላል። በመላ ሀገሪቱ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የ17 ዓመት ሰቆቃ ለፈጸመ የደርግ ወንጀለኛ ግን በጥቅስ ውስጥ የሚገኘው አባባል ተስማሚ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ጥያቄውን እንኳ ለማንሣት ቦታውም አይደለም። የዚህ ዓይነት አስተያየት የሚሰጥ ሰው ከደርግ ዘመን በኋላ የተወለደ ወይም ቀደም ሲል ተዎልዶ በህጻንነት ዕድሜ ላይ የነበረ ሰው መሆን አለበት። ለነገሩማ ህጻንስ ቢሆን የደርግ ጥይት ያልዳሰሰው ቤት በኢትዮጵያ ዉስጥ መች ይኖራል፤ ወይም ደግሞ ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት አሁን ያለው የዘረኛው መንግሥት ራሱ ወይም ተወካዩ መሆን አለበት።

ከዚህም ሌላ፤ የደርግ ታሣሪዎች የይቅርታ ጥያቄ የፍትህ ጉዳይ ነው፤ አንድ ሰው ለሞት የሚያደርስ ወንጀል ፈጽሞ፤ ባደረሰውም ጥፋት በሕግ ፊት ለፍርደ ቀርቦ የጥፋቱ ዓይነትና መጠን የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እሥራት በሚደርስ ቅጣት ከተፈረደብት፤ ወደሌላ ደረጃ አይሄድም፤ ሲበዛ ቢውል ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ፍርድ ቤት እሥራቱን በአመክሮ ሊቀንስ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖር ሆናል እንጅ፤ በይቅርታ መለቀቅ አይችልም። እነዚህ ሰዎች እኮ የታሠሩት ከሰባዊ ርኅራኄ ውጭ በጭካኔ እያሌ ህዝብን በመጨፍጨፍ ማለትም በመግደል ወንጀል ነው፤ ወንጀሉ የፖለቲካ ወይም በሌላ አይደለም፤ ስለዚህ እነሱ ይቅርታ መጠየቅም ሆነ በእንሱ ስም ሌላ ተወካይ ምህረት እንድደርግላቸው ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፤ መብቱም የላቸውም፤ ከሆነ ደግሞ፣ ስላደርሱት የሰው ልጅ ጭፍጨፋና በሃገሪቱ ላይ ስለፈጸሙት ኢሰባዊ ድርጊት የኢትዮጵያን ህዝብ የቅርታ እንዲያደርግላቸው መጠይቅ ይችሉ

የነበረው ከፍርድ በፊት ነበር። በዳኝነት በኩል ከተሔደ፤ ወንጀል ወንጀል ነው፤ አንድ ብር የሠረቀና አንድ ሚሊዮን ብር የሰርቀ ቅጣቱ በፍርድ እኩል ነው። ነፍስ ማጥፋትም እንደዚሁ ነው፤ እነዚህ ሰዎች እኮ ኢትዮጵያን የሰው ድሀ አደርገዋት ነው የወደቁት፤ ስንቱ ምሁር፤ ለጋ ሕጻናት ወጣት ሴቶችና ወንዶች፤ ዐዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችና ለወድ ሀገራቸው በየበረሃው ሲዋደቁ ኖረው በጡረታ የዕድሜ ክልል የነበሩ የሃገር ተከላካይ ወታደርና በሥነምግባራቸው እንከን የሌላቸውን ምርጥ መኮንኖችንና ታልላቅ መሪዎችን፤ ከዳር እስከዳር ጥርግርግ አድርጎ ፈጅቶአል፤ሰዉ አልቋል፤ የደርግ ጁንታ ለ 17 ዓመታት ሃገሪቱን ቀጥቅጦ መግዛቱ ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን ያለ ሰው፤ ያለ ተከላካይ ጥሎ ሄድዋል፤ ምን ያረጋል፤ "የቤቴ መቃጠል ለትኋኔ በጀኝ" እንድሚሉት ሆነና ወያኔ/ኢህዴግ አድፍጦ ከተቀመጠበት ጫካ በመውጣት ስተት ብሎ ከሚኒልክ ቤተመንግሥት ለመግባት የቻለው ይሁ ደርግ ለአሥራ ሰባት ዓመት ባካሔደው የግድያ ዘመን የተቀጠቀጠው ኅዝብ የሞተው ሞቶ ያልሞተው ደግሞ ወኔው ተሟጥጦ ስለነበረባዶ ሜዳ ሆኖ ስላገኘው ነው። ይህ ዕውነታ ከቶ ሊዘነጋ አይገባውም።

የቀይ ሽብር ውንጀለኞች፤ የቀድሞው አረመኔ አገዛዝ ባለሥልጣናት፤ የስንት መቶ ሽህ ንጹህ ዜጋ ደም እንደጎርፍ የፈሰሰው በሰው በላው በመንግሥቱ ኃ/ማሪያም መሪነት ኢትዮጵያን ለ 17 ዓመት የገዛው የባለ 120 ንጉሦች ደርግ የተባለው ጉግ ማንጉግ መንግሥት ነው። ደርግ ባደረሰው የሰው ዘር ጭፍጨፋ ገና በ ዓለም መንግሥታት የፍርድ ሸንጎ የሚቀርብበት ነግሮች እየተመቻቹ ባለበት ባሁኑ ወቅት ከሥር ቤት እንዲለቀቁ ለማድረግ የሚደረገው መሯሯጥ ወያኔ እራሱ ከፊተኛው ባላነስ እንዲያውም በ ዕጥፍ የሚበለጥ የሀገር ማውደም ዘመቻ ላይ ስለሚገኝና ያው የማይቀረው ጊዜ ሲደርስ (እርሱም ሩቅ አይሆንም) ከሥልጣኑ ወርዶ እሥር ቤት እንደሚወረወር ስለሚያውቅ ለራሱ በር ለመከፈት ለማመቻቸት ያለው ለመሆኑ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊገነዘበው ይገባል።

ለማጠቃለል ያህል፤ በመጀመሪያ ይቅርታ ተጠያቂው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፤ የ60 ባለሥልጣኖች ቤተሰብ ብቻ አይደለም። ከላይ እንደተጠቀሰው የበደሉና የግፉ መጠን እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ለታሳሪዎቹ ይቅርታ ማድረግ ቀርቶ በህይወት እሥራት እንኳ እንዲቆዩ መደርጉ የጥይት ራት በመሆን ልጁን፤ ወንድሙንና እህቱን እንደዚሁም አባትና እናቱን ላጣው አያሌ የኢትዮጵያ ወገን ተጨማሪ በደል ነው። የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ራሴ ከእኔ ዘንድ አስቀምጬ አሳድጌና አስተምሬ ለቁም ነገር ያበቃሁትን ታናሽ ወንድሜን በአረመኔው በመላኩ ተፈራ እጅ ከፊቴ ላይ በጥይት ተደብድቦ ሞቶብኛል፤ መሞቱም ብቻ አይደለም እቤቴ ተቀምጬ ለማልቀስ እንኳ የተከለከልኩበት ጊዜ ነው፤ ታዲያ እንዴት አድርጌ ነው ይህንን ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት በይቅርታ ለማየት የምስማማው? የደረሰብት ብቻ ይፍረድ!!

ናመይሣው

[ከኢትዮሚድያ (Ethiomedia.com)
February 5, 2011]